የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን (ማርች 8) አስመልክቶ ንቅናቄ ለመፍጠር የተዘጋጀ የውይይት ሰነድ

‹‹የሴቶች የቁጠባ ባህል ማደግ ለህዳሴያችን መሰረት ነው!››

የካቲት/2009 ዓ. ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር

ራዕይ

በ2017 የኢትዮጵያ ሴቶች በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና በባህል መስኮች የሴቶች እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተረጋገጠባት፣ የህፃናት መብትና ደህንነት የተከበረባት እና የስርአተ-ጾታ እኩልነት የሰፈነባት እና የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ተገንብቶ ማየት::

ተልዕኮ

የሴቶችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስኮች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ የህጻናትን ማህበራዊ ደህንነት ለማስጠበቅ፣ አለምና አህጉር አቀፍ ስምምነቶችን ተፈጻሚ ማድረግ፣ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ ሀገር አቀፍ ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎች ማዘጋጀት፣ በሴቶችና በህጻናት ጉዳይ የሚሰሩ አካላትን ማስተባበርና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር የአቅም ግንባታ ስራ መስራት፣አፈጻጸማቸውንም በመከታተልና በመገምገም ተፈጻሚ ማድረግ፤

እሴቶች

- የህግ የበላይነትን
- የስርአተ-ጾታ እኩልነት
- የህጻናት መብትና ደህንነት
- ግልጽነትና ተጠያቂነት
- ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት
- መልካም ስነ ምግባር
- የቡድን ስራ

በውስጥ ገጾች

መግቢያ 2

ምዕራፍ አንድ

1. የሴቶች ጭቆና በአለም አቀፍ፣ በአህጉርና በሀገር ደረጃ..................3

1.1 በአለም የሴቶች ጭቆና እንቅስቃሴዎች..........................3

1.2. በአፍሪካ የሴቶች ጭቆናና እንቅስቃሴ..........................4

1.3. በኢትዮጵያ የሴቶች ጭቆና እንቅስቃሴዎች......................4

ምዕራፍ ሁለት

2.1. ሴቶችና ህገ- መንግስቱ..6

2.2. በህገ መንግስቱ የሴቶችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ በተሰሩ ስራዎች የተገኙ ውጤቶች..7

2.3 ሴቶችና ቁጠባ..10

2.4. በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት.......... 10

2.5. የአረንጓዴ ልማትና የከተማ ውበት.....................................11

2.6 ሴቶችና የልማት ቡድን..12

2.7. ሴቶች ሰላምና ዲሞክራሲ..12

ምዕራፍ ሦስት

3. የሴቶችን መብቶች ከማረጋገጥ አኳያ ያሉ ክፍተቶችና ቀጣይ አቅ ጣጫዎች..14

3.1 የሴቶችን መብቶች ከማረጋገጥ አኳያ ያሉ ክፍተቶች...............14

3.2. ቀጣይ አቅጣጫዎች..15

3.3. ማጠቃለያ..16

መግቢያ

ሴቶች በአለማችን፣ በአህጉራችንና በሀገራችን በነበሩ ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ችግሮች ምክንያት ለብዙ ዘመናት ጉዳት ሲደርስባቸው የቆየ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በፖለቲካዊ መስክ ሴቶች ወንዶች ያላቸውን ፖለቲካዊ መብቶች ያጡበት፣ መምረጥ እና መመረጥ መብቶችን በህግ ደረጃ እንዳይኖራቸው የተደረገበት፣ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥም ተሳትፎአቸው የተገደበበት እንደነበር የምናስታውሰው ነው፡፡ በኢኮኖሚው መስክ ሴቶች ተሳትፎአቸው እንዲገደብ ተደርጎ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና ሀብት የማፍራት፣ የማስተዳደር እና ሌሎች መብቶች እንዳይኖራቸው ተደርጎ ቆይቷል፡፡ በማህበራዊ ህይወታቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የታዩበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በአጠቃላይ ሴቶች ላይ ሲደርሱ የነበሩ ችግሮች ዘርፈ ብዙ እና ጉዳቱም በጣም ከፍተኛ መሆኑን ታሪክ የሚያረጋግጠው ሀቅ ነው፡፡

ይሁንና ሴቶች ላይ ሲደርሱ የነበሩ በደሎችና ግፎችን ሴቶች አሜን ብለው የተቀበሉበት ጊዜ አነስተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በደሎችና ግፎቹን ለማጥፋት እንዲያስችላቸው የተለያዩ መልክ ያላቸው ትግሎችን ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በመጣ ለውጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሴቶችን መብት እና ጥቅም ሊያስጠብቁ የሚያስችሉ የተለያዩ ስምምነቶች እና ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች ወጥተው ሀገራትም እነዚህን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች የሀገራቸው ፖሊሲ፤ስትራቴጂ እና ህግ አካል በማድረግ እንዲሰሩ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ እያደረጉም ይገኛሉ፡፡

የሀገራችን ሴቶች እንደ ሌሎች የዓለማችን ሴቶች ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ በደሎች እና ጉዳቶች ሲደርስባቸው ቆይቷል፡፡ ሀገራችን ውስጥ በነበሩት ጸረ-ዴሞክራሲያዊ መንግስታት ምክንያት ሴቶች ላይ ሲደርስ የነበረው በደል ድርብ እና ድርብርብ የነበረ ሲሆን ይህን በደል ለማጥፋት እንዲያስችላቸው ሴቶች በተለያየ አደረጃጀቶች ውስጥ በመሆን ሲታገሉ ቆይተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የህዝቦችን መብት እና ጥቅም የሚያስከብር ዴሞክራሲያዊ ፌደራላዊ የመንግስት ስርዓት በሀገራችን እንዲኖር ማድረግ ላይ ሴቶች የነበራቸው ተሳትፎ እጅግ በጣም ከፍተኛ እና በታሪክ ተመዝግቦ የሚገኝ ነው፡፡

በዚህ አግባብ የተገኘውን ውጤት ወደ ተግባር ለመቀየር እንዲያስችል ሀገራችን ምቹ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማበጀትና ለተግባራዊነቱም የተለያዩ መዋቅራዊ አደረጃጀቶችንና በጀት በመመደብ ዘርፈ-ብዙ ተግባራት ሲከናነወኑ ቆይተዋል፤ እየተከናወኑም ይገኛሉ፡፡ በዚህም አግባብ በሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ረገድ አበረታች ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡

በአለማችን በፊት የነበሩ ቀድምት ሴቶች ዛሬ ለደረስንበት ደረጃ የከፈሉትን መስዋዕትነት በመዘከር ለበለጠ ስራ ለመነሳት ሴቶችን የተመለከቱ ሁነቶች በሀገርና በአለምዓቀፍ ደረጃ ይከበራሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ አለም አቀፍ የሴቶች ቀን አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም በሀገራችን በዘንድሮው ዓመት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ106ኛ በሀገራችን ለ41ኛ ጊዜ የሚከበረውን በዓል የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ፤ሴቷን በኢኮኖሚ ለማብቃትና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎዋን ለማሳደግ እድሎችን በሚሰጥ መልኩ ከፌዴራል እስከ ቀበሌ የአስተዳደር እርከን ብሎም እስከ ልማት ቡድን ድረስ የቁጠባ ባህል ማደግ ለሀገራዊ እድገት እና ለሴቶች ኢኮኖሚያዊ ብቃት መረጋገጥ መሰረት መሆኑን ለማስገንዘብና የተሻለ አፈጻጸም ላላቸው እውቅና ለመስጠት "የሴቶች የቁጠባ ባህል ማደግ ለህዳሴያችን መሰረት ነዉ!>> በሚል መሪ ቃል በተደራጀ የንቅናቄ ፕሮግራሞች ለማክበር ታቅዷል፤ ከዚህም ጎን ለጎን ሴቶች በከተሞች ልማትና ሀገራችን እየገነባች ያለውን የህዳሴ ግድብ ከግብ ለማድረስ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያደርጉ ፕሮግራሞችን ማካሄድ አንዱ የኩነቱ አካል ይሆናል፡፡ ስለሆነም ለንቅናቄው ይረዳ ዘንድ ይህ ጽሁፍ ተዘጋጅቷል፡፡

ምዕራፍ አንድ

1. የሴቶች ጭቆና በአለም አቀፍ፣ በአህጉርና በሀገር ደረጃ

1.1 በአለም የሴቶች ጭቆና እንቅስቃሴዎች

ሴቶች በተለያዩ የተዛቡ አመለካከቶች የባህል ተጽእኖዎች ምክንያት በህብረተሰብ ውስጥ የሚገባቸውን ቦታ ይዘው ሰብዓዊ መብቶቻቸው ተጠብቆላቸው በሀገር ልማት ውስጥ ሊያደርጉ የሚችሉትንና የሚገባቸውን ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚገድቡ አሰራሮችና ድርጊቶች ነበሩ፡ ፡ ዲሞክራሲያዊ የሆነ የመንግስት ስርዓት ይከተላሉ በሚባሉ አብዛኞቹ የምዕራብ ሀገራት እና አሜሪካንን ጨምር የሴቶችን መብት እና ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችሉ በቂ የሆኑ የህግ ማእቀፎችና እና አደረጃጀቶች አልነበሩም። ይልቁንም የነበረው ፓለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መዋቅር የሴቶችን መብት እና ጥቅም የማያካትት እና የሚያገል ነበር።

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተለያዩ ፋብሪካዎች ይሰሩ የነበሩ ሴት ሰራተኞች ላይ ይደርስ የነበረው የመብት ረገጣና ጭቆና ሴቶችን ለትግል አነሳስቷቸዋል። በተለይ በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎችና በማምረቻ ቦታዎች የሚሰሩ ሴት ሰራተኞች ለጤና በማይስማማ የስራ ቦታ ይመደቡ የነበረ ከመሆኑም በላይ እጅግ አነስተኛና የእለት የኑሮ ህይወታቸውን ለመምራት በማያስችል ክፍያ ይሰቃዩ ነበር።

በዚህም የተነሳ በሴቶች ዙሪያ ይታዩ የነበሩ ማንኛውም ጭቆናዎች እንዲወገዱ በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በአውስትራሊያ በሴቶችና በወንዶች እንዲሁም በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴዎች ተጀመሩ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጠናቀቅ በኃላ የተመሰረተው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በመቋቋሚያ ቻርተሩ ላይ የሴቶችን መብትና ጥቅምን በተመለከተ ሰፋ ያሉ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል። የድርጅቱ ግብ ምን እንደሆነ በመግቢያው ላይ ሲያስቀምጥ "to reaffirm faith in fundamental human rights, in the dignity and worth of the human person, [and] in the equal rights of men and women" መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን የማረጋገጥ፣ የሰዎችን ክብር በተለይም በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን እኩል ባለመብትነት ማረጋገጥ እንደሆነ አስቀምጧል።

በሌላ መልኩ ቻርተሩ በአንቀጽ 1፣13 እና 55 ላይ ሰብዓዊ መብቶች ለሁሉም የሰው ልጆች እኩል ሊከበሩ እና በሴቶችና በወንዶች መካከል መድሎ የማይፈቀድ እንደሆነ ደንግጓል።ከቻርተሩ በኃላ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና ሌሎችም ዓለምዓቀፍ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ የሴቶች ጉዳይ ከምንጊዜዉም በላይ ምላሽ የሚሰጡ ምቹ ሁኔታዎች ማመቻቸት ጀመሩ ለአብነት ያህል በ1948 ፆታን መሰረት ያደረገ አድልዎ እንዳይኖር የሚያደርግ ዩኒቨርሳል የሰብአዊ መብት ዲክለራሽን፤ በ1966 የተደነገጉት የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በሴቶች እና በወንዶች መካከል መድሎ የሚፈጽሙ ህጎችና አሰራሮች ተቀባይነት እንዳይኖራቸው፤ እኩልነትን ለማረጋገጥ እንዲያስችል መንግስታት የተለያዩ ስራዎችን ማከናወን የሚጠበቅባቸው መሆኑ እና ሌሎች ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዘው እንዲወጡ ተደርጓል። በተጨማሪም በ1975 በጾታ ልዩነት ምክንያት በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጭቆና የማስወገድ ዋና ዓላማን ያነገበ "ዓለምዓቀፍ የሴቶች አመት" የታወጀ ሲሆን በ1979 ደግሞ በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም አድሎ የሚያስወግድ ስምምነት "The Convention on the Elimination of All Forms of Discrimination against Women" ጸድቆ ተግባራዊ ሆኗል። በዚህ አጋጣሚ የተወሰደዉ እርምጃ ይበል

የሚያስኝ ቢሆንም በእንቅስቃሴዉ መጠን የተገኘዉን ዉጤት ስንመለከት ግን በጣም አነስተኛ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

1.2. በአፍሪካ የሴቶች ጭቆናና እንቅስቃሴ

አፍሪካም የሴቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ የተነፈጉበት እንደነበረ በተለያዩ አለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ መዛግብት ተሰንደው ይገኛሉ፡፡ ይህን ሁኔታ ለመቀየር የአፍሪካ ሴቶች አህጉሪቱን ከአውሮፓዊያን የቅኝ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት ያበረከቱት እና የተጫወቱት ሚና ትልቅ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአፍሪካ የሴቶች ትግል በመለው አፍሪካ ተመሳሳይ የሆነ ፍላጎት እና አመለካከት እንዲኖራቸው ከማድረጉ ባሻገር የነበረው አመለካከትና ድርጊት ሴቶችን በእኩል አይን የማያስተናግድ በመሆኑ ሴት አፍሪካውያን ለመብታቸው እንዲቆሙ አድርጎቸዋል፡፡

አብዛኞች የአፍሪካ ሴቶች እንዲታገሉ ካነሳሷቸው አያሌ ምክንያቶች መካከል የእኩልነት ጥያቄ፣ ፍትህ እንዲረጋገጥ መፈለግ፣ ማህበራዊ እውቅና መፈለግ፣ፖለቲካዊ እኩልነት እንዲረጋገጥ መፈለግ፣ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ፍትሕ እና የህግ ጥበቃ እንዲኖራቸው መፈለግ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- በናይጀሪያ በሴቶች የሚመራ ብዛት ያላቸው ተቃውሞዎች ሲደረጉ የነበሩት ወጥ ያልሆነና የተዛባ የማህበረ ፖለተካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ድልድል በወንዶች እና በሴቶች መካከል በመኖሩ የተነሳ ነበር፡፡ በተመሳሳይ በሩዋንዳ የሩዋንዳውያን ሴቶች ትግል በመጀመሪያ በፐብሊክ ሴክተሮች ውስጥ በወንዶች እና በሴቶች መካከል የነበረውን ክፍተት ለማጥበብ በመሻት የነበረ ፍላጎት በማሳደራቸው ሳቢያ ሲሆን ቀስ እያለ በአገሪቱ የስርዓት ጦታ ዝኩልነት እንዲሰፍን ለማድረግ ወደሚያስችል የትግል እንቅስቃሴ ተሸጋግሯል፡፡ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት እንዲመጣ እነዚህ ትግሎች ጥቂትና ፋና ወጊ በሚባልላቸው የአፍሪካ የሴቶች የተካሄዱ እንቅስቃዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ትግሎች ምክንያት በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት የህገ-መንግስት ለውጥ የተካሄደበትና የሴቶች ጉዳይም በህግ ማዕቀፍ ጭምር ተካቶ ሁለንተናዊ መብታቸውን በሚያከብር መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም ያረጀ ያፈጀ የነበረውን የማህበረ- ፖለቲካዊ መዋቅር ከስሩ በመንቀል የሴቶች ጉዳይ ትኩረት እንዲሰጠው አድርጓል፡፡

የአፍሪካ ህብረት መቋቋሚያ ሰነድን መነሻ በማድረግ የወጣው የአፍሪካ የሰብዓዊ መብት እና የህዝቦች ቻርተር "African Charter on Human and Peoples' Rights" ላይ የሴቶች እኩልነት መረጋገጥ እንደሚኖርበት ሲገልፅ ጸታን መነሻ ያደረግ መድሎ እና አግላይነት ሊቀር(አንቀጽ 2) እንደሚገባው ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቻርተሩን ይበልጥ ወደ ተግባር ለመቀየር እንዲያስችል አ.ኢ.አ በ2003 የፀደቀው የሴቶችን መብት ለማረጋገጥ የሚያስችል ፕሮቶኮል(ማፑቱ ፕሮቶኮል) ወይም "Protocol To The African Charter On Human And Peoples' Rights On The Rights Of Women In Africa" እየተተገበረ ይገኛል፡፡

1.3. በኢትዮጵያ የሴቶች ጭቆና እንቅስቃሴዎች

አገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ መንግስታዊ ቢሆንም ሥርዓቶችደግሞ የሴቶችን ጥያቄዎች በመፍታት ረገድ ባመዛኙ በተለይ ተቀራራቢነት ይስተዋልባቸው ነበሩ፡፡ በአገራችን ተጨባጭሁኔታ የሴቶች ጭቆና መሠረቱ ወንዶች ሳይሆኑ ሥርዓቱ እንደነበር በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

የነበሩ ሥርዓቶች በሴቶች ላይ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጭቆናዎችን ሲያደርሱ መቆየታቸው የሚታወስ ነው፡፡ ጭቆናው በሁለንተናዊ መልኩ የሴቶችን የበታችነት የሚያንፀባርቅ መዋቅራዊ መሠረት ያለውና እጅግ ሥር የሰደደ እንደሆነ በትጋት የተንቀሳቀሱና የተገበሩ ነበሩ፡፡

በመሠረቱ ፆታዊ ጭቆናው ምንጩ መደባዊ ጭቆና የነበረ በመሆኑ የአጠቃላዩ የሕብረተሰብ መደባዊ ጭቆና አካል ነበር ማለት ነው። ይሁን እንጂ የሴቶች ጭቆና ፆታዊ መልክም የነበረው ነበር። ስለሆነም ድርብ ጭቆና ነበር። በኢትዮጵያ ሴቶች ከጭቁን ወንድሞቻቸው ጋር ሆነው በፀረ ፊውዳሊዝምና ገዥ መደቦች ትግል በተማሪነት፣ በአርሶ አደርነት፣ በፋብሪካ ሰራተኝነት ወዘተ ታላቅ ተጋድሎ አካሂደዋል።

በ1966ቱ አብዮት ከመጀመሪያው አንስቶ የፖለቲካ ሂደት የዳር ተመልካቾች እና መጨቆንና መበዝበዝን ባለመቀበል ለነፃነታቸውና ለሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች እኩልነትና መብት ታግለዋል። ለአብነትም የፖለቲካ እንቅስቃሴ በተፈጠረበት በመጋቢት 08 ቀን 1966 ዓ.ም ቁጥራቸው ወደ ሶስት ሺህ የሚጠጋ ሴቶች ጭቆናዎችና በደሎች እንዲቆሙ እንዲሁም ለእኩል ስራ ከወንዶች እኩል ክፍያ እንዲኖር ለመጠየቅ በንጉስ ነገስቱ ቤተ-መንግስት ፊት ለፊት ሰላማዊ ሰልፍ አደርገዋል።

በተጨማሪም ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሻለ የጤና ክብካቤና የትምህርት እድል፣ የተሻለ የስራ እድል፣ የተሻለ ክፍያና የስራ አካባቢ ጥያቄ ያነገቡ ሰላማዊ ሰልፎችን ያደራጁና ያስተባበሩ የሴቶች ንቅናቄዎችን አስተናግዳለች። ሆኖም ግን ሴቶች በሙያ ማህበራት (በሰራተኛ ማህበራት) የተደራጁ ስላልነበሩ ሰላማዊ ሰልፎቻቸው ምንም ዓይነት ተጨባጭ ውጤቶች አላስገኙም። ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት/ደርግ/ ስልጣን ከያዘ በኃላ የኢትዮጵያ ሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ በመባል የሚጠራ ትንሽ ኮሚቴ አቋቋመ። ይህ ቡድንም በአዲስ አበባ ከተማ ሴቶችን በማንቀሳቀስ ሴሚናሮችና የፖለቲካ ውይይት መድረኮችን አዘጋጅቷል። ይህ በዓይነቱ የመጀመሪያው የሆነው ኮሚቴ፤ምንም እንኳን አመርቂ ውጤቶችን ባያስመዘግብም የሴቶችን የፖለቲካ ንቃት ደረጃን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት አከናውኗል። ሆኖም ገና ብዙ ሳይራመድ ሴቶቹን በተለያየ ሰበብ አስባብ ውጤታማ እንዳይሆኑ ሆነዋል በዚህ ሳቢያ የኮሚቴው አባላት ሳይቀሩ አንዳንዶቹ አገራቸውን ትተው ለመሄድ ተገደዋል፤ የተወሰኑት ብረት አንስተው የትጥቅ ትግሉን ሲቀላቀሉ ቀሪዎቹቹ ደግሞ ወደ ወህኒ ቤት ተወርውረዋል።

የደርግ መንግስት ሴቶች ላይ ሲያደርስ የነበረው ግፍ አሰቃቂ ነው። ለእኩልነት፤ ለህዝባዊ መንግስት፤ ከብሔር ጭቆና ለመላቀቅ ሲታገሉ የነበሩ ልጆችን ከእናት እቅፍ በማውጣት ሲጨፈጭፍ የነበረው ደርግ ይህ አልበቃ ብሎት ልጆቻቸው ለጦርነት እሳት እንዲማገዱ ያስገድድ ነበር። በዚህም ምክንያት እናቶች ልጆቻቸውን ሴቶች ባሎቻቸውን በማጣት ደርግ የሚያደርስባቸውን በደል አሜን ብለው ተቀብለው የተዉ ሳይሆን ከሌሎች ታጋዮች ጋር በመሆን ሰው በላ የሆነው ስርዓት እንዲገረሰስ የማይተካ ሚና ተጫውተዋል። በመጨረሻም የደርግ ስርዓትን በመጣል ሀገሪቱን ወደ ዲሞክራሲ ምዕራፍ በማሸጋገር ሂደት ትልቅ መስዋዕትነት ከፍለዋል።

የደርግን ስርዓት መውደቅ ተከትሎ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት በሚቀረፁበትና በሚፀድቁበት ወቅት ንቁ ተሳታትፎ በማድረግ በመሳተፍ የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተዋል። በመቀጠልም ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ በተከታታይነት በተካሄዱ አምስት ሀገራዊና ክልላዊ እንዲሁም የወረዳና የቀበሌ ማሟያ ምርጫዎች በመምረጥና በማስመረጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎ በማድረግ የሀገራችን የዲሞክራሲ ግንባታ እዲጎለብት ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል በማበርከት ላይም ይገኛሉ።

ምዕራፍ ሁለት

2. ሴቶች ጭቆናን ታግለዉ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ፖለቲካዊ መስኮች ያገኟቸዉ ድሎች

2.1. ሴቶችና ህገ- መንግስቱ

የፌደራል ስርዓት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በእኩልነትና በአንድነት ሀገር ለመገንባት ለያዙት ዓለማ መሳካት ያለው ፋይዳ ትልቅ ነው። በመሆኑም በፈቃደኝነትና እኩልነት ላይ የተመሰረተ የጋራ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችል የፌዴራል ስርዓት በመገንባት ላይ ይገኛል። ሴቶች በፊት በነበረው ስርዓትና በማህበረሰቡ ባሉ ልማዳዊ አመለካከቶችና ድርጎቶች ለተለያዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሰለባና በማህበራዊና ኢኪኖሚያዊ መስኮች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ ሳይሆኑ ቆይተዋል አሁንም ቢሆን ክፍተት እንዳለ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢፌዴሪ ህገ መንግስት የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ መብቶችና ጥቅሞች ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ድንግጌዎችን ይዟል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝቦች የቃል ኪዳን ሰነድ የያዘው ህገ-መንግስታችን ያጎናፀፋቸው ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ዋና መነሻ በማድረግ መንግስት የቀረፃቸው ልዩ ልዩ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች እንዲሁም የደነገጋቸው ህጎች በስራ ላይ መዋል በመቻላቸው የሴቶች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ይገኛል።

በሀገራችን ለሴቶች ጉዳይ ትኩረት በመስጠት ህገ መንግስቱ ከመዉጣቱ በፊት የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ በ1986 ዓ.ም ተቀርፆ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የሴቶችን ጉዳይ የሚከታተል በፌዴራል በክልሎች እና እስከ ታቸኛው ባለው የአስተዳደር እርከኖች መንግስታዊ መዋቅር ተዘርግቷል። በተጨማሪም የሴቶችን ጉዳይ ፖሊሲ ወደ መሬት ለማውረድና የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የከተማ፣የገጠር እና የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ሴቶች ሁኔታዎች ያገናዘቡ የልማት ፓኬጆች ተቀርፀው ተግባራዊ ሆነዋል በተጨማሪም ፓኬጆችን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ወደ ስትራቴጂ እንዲያድግ ተደርጓል። በርካታ በየደረጃው የተገኙ የልማት ፍሬዎችን በማጣጣም ላይ ይገኛሉ። ህገ-መንግስቱ ለሴቶች የሰጣቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ይቀርባል።

2.1.1. ፓለቲካዊ ጉዳዮች

የሴቶችን ፓለቲካዊ መብቶችና ጥቅሞች ለማረጋገጥ እንዲያስችል በህገ-መንግስቱ ከሰፈሩ ድንጋጌዎች መካከል ከዚህ የሚከተሉት ይገኙበታል እነዚህም፡-

- በአንቀጽ 25 ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፡፡ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፓለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡

አንቀጽ 35(1) ሴቶች ይህ ሕገ-መንግስት በአረጋገጣላቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡

አንቀጽ 35(3) ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ጠባሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ አሻራ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ

የመሆን መብት አላቸው። በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግስት እና በግል ተቋሞች ወስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው።

መንግስት በዚህ አግባብ ያሉትን መብቶች ወደ ስራ ለመቀየር የሚያስችለውን የተለያዩ ፓሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና የህግ ማዕቀፎችን በማውጣት ሲሰራ ቆይቷል።

2.1.2. ኢኮኖሚዊ ጉዳዮች

ህገ-መንግስቱ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ መብቶችና ጥቅሞች ለማረጋገጥ እንዲያስችሉ ከዚህ የሚከተሉት ድንጋጌዎች አስፍሯል እነዚህም-

- በአንቀፅ 32/1 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ . . . በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነፃነት አለው።
- በአንቀጽ 32/2. . . ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ወደ ሀገሩ የመመለስ መብት አለው
- አንቀጽ 35/ 6 እና 7፣ ሴቶች ብሔራዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ በዕቅዶች እንዲሁም በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም፣ በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ሀሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው። ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው።
- አንቀጽ 42፣ ሴቶች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብት ተረጋግጧል።
- በአንቀጽ 41 ሴቶች ልክ እንደማንኛውም የሀገር ዜጋ በነጻነት በመረጡት የኢኮኖሚ ተግባራት የመሰማራት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፣
- በአንቀጽ 89(7) መንግስት በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ከወንዶች ጋር በእኩልነት የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሃላፊነት አለበት።

2.1.3. ማህበራዊ ጉዳዮች

የሴቶችን ማህበራዊ መብቶችና ጥቅሞች ከማረጋገጥ አኳያ ህገ-መንግስቱ ከዚህ የሚከተሉት ድንጋጌዎች አካቶ ይዟል፡-

አንቀጽ 34(2) ጋብቻ በተጋቢዎች ነጻና ሙሉ ፍቃድ ላይ ብቻ ይመሰረታል።

አንቀጽ 35(9) ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው። ይህ በሕገ-መንግስቱ ላይ የተደነገገውን የሴቶች መብት ሙሉ በሆነ ደረጃ ለመተግበር እንዲቻል መንግስት የተለያዩ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎችን በመቅረፅ በስራ ላይ እንዲውሉ አድርጓል። የቤተሰብ ህግ እና የወንጀል ህግ እንደ አብነት የሚጠቀሱ ናቸው። በቤተሰብ ህጉ ላይ ሴቶች ጋብቻ በሚፈጽሙበት ወቅት፣ በጋብቻ ህይወታቸው እና ጋብቻው በሚፈርስበት ወቅት ከወንዶች እኩል መብት ያላቸው መሆኑን ያረጋገጠ ሲሆን በዚሁ አግባብ ሴቶች ለብዙ ዘመናት ሲታገሉለት የነበረውን ማህበራዊ እኩልነት ለማረጋገጣ ያለው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ ነው። በሌላ በኩል የወንጀል ህጉ ለሴቶች በህገ-መንግስቱ የተቀመጡትን መብቶች ለማረጋገጥ እንዲያስችል በሴቶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ድርጊቶች ማለትም አስገድዶ መድፈር፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ግርዛት እና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የወንጀል ተግባራትን መሰረት በማድረግ የሴቶችን መብቶች ለማስጠበቅ በሚያስችል መልኩ ተሻሽሎ አምርታዊ ድንጋጌዎችን ይዞ ወጥቷል።

2.2. በህገ መንግስቱ የሴቶችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ በተሰሩ ስራዎች የተገኙ ውጤቶች

ሕገ-መንግስት ስራ ላይ ከዋለበት ከ1987 ወዲህ የሴቶችን መብት እና ጥቅም ከማስከበር ጋር ተያይዞ በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ተስፋ ሰጪ የሆኑ ውጤቶች ተመዝግበዋል። በፓለቲካዊ፣

ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መስኮች የተገኙ ውጤቶች ከዚህ በሚከተለው አግባብ ቀርቧል፡፡

2.2.1. ፓለቲካዊ ውጤቶች

ሕገ-መንግስቱ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ሴቶች ተጠቃሚ ከሆኑባቸው ጉዳዮች አንዱ የፓለቲካ ተሳትፎ ሲሆን በዚህ ረገድ የተጠቃሚነት ደረጃቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡ የመንግስት አካላት በሚባሉት የህግ አውጪ፣ ሕገ-አስፈጻሚ እና ህግ ተርጓሚ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ እየጨመረ ነው፡፡ የዚህ ተሳትፎ ዓይነት በሁለት መልኩ የሚገለጽ ሲሆን በአንድ በኩል በመንግስት አካላት በመንግስት ሰራተኛነትም ሆነ በአመራር ደረጃ ቁጥራቸው በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች በውሳኔ ሰጪነት ቦታ ላይ መቀመጥ እንደዚሁ እያደገ መጥቷል፡፡

በ2007 በሀገራችን በተካሄደው ሀገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ሲታይ በፌዴራል ደረጃ በሚገኘው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሚገኙ መቀመጫዎች ውስጥ ያህሉ 38.8 በሴቶች የተያዘ ሲሆን የክልል ምክር ቤት መቀመጫዎች ደግሞ 40.2 ከመቶ የሚሆነው በሴቶች የተሸፈነ ነው፡፡ በየአካባቢው በሚገኙ ምክር ቤቶች ውስጥም የሴቶች ድርሻና ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በስራ አስፈጻሚው አካል ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በከፍተኛ አመራር ደረጃ /በሚኒስትርነት፤ በሚኒስትር ዲኤታነት፤ በዋና ዳይሬክተርነት እና በመሳሰሉት/ እየጨመረ የመጣ ነው፡፡ በፌደራልም ሆነ በክልል በሚገኙ የዳኝነት አካላት ወስጥ የዳኝነት ስራ ላይ የሴቶች ተሳትፎም የጨመረ መሆኑ በተጨባጭ የሚታይ ሀቅ ነው፡፡

ሴቶች በሕገ-መንግስቱ ዋስትና ባገኘው የመደራጀት መብት በመጠቀም የተለያዩ ጸታዊ እና ሞያዊ አደረጃጀቶች በመዘርጋት እና በማሳተፍ የሚፈለገውን ውጤት በተደራጀ መልክ ለማምጣት ያላቸው እንቅስቃሴም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡

2.2.2. ኢኮኖሚያዊ ውጤቶች

የኃይል አቅርቦትና ተስማሚ የገጠር ቴክኖሎጂ በማስፋፋት ረገድ የተከናወኑና እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ከማንም በላይ ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችሉ መሆናቸው ላይ ከሴቶች በላይ ምስክር አያሻውም። ባለፉት አመታት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሽፋኑ እጅግ ዝቅተኛ ከነበረበት 54.4% አድገት ማሳየቱና ይህም በርካታ የገጠር ከተሞችንና ቀበሌዎችን ተጠቃሚ ማድረግ የጀመረ በመሆኑ መጀመሩ በዋናነት በገጠር ለሴቶች ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት ለማስፋፋት የሚያስችል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።ለአብነትም በገጠር የወፍጮ አገልግሎትን ለማስፋፋት እንደ ቀድሞ ባለሀብቱን ብቻ መጠበቅ ሳያስፈልግ በአንዳንድ አካባቢዎች የሴቶች ማህበራት፣ የአርሶአደር የህብረት ስራ ማህበራት ራሳቸው አገልግሎቱን በማስፋፋት ሂደት ላይ ይገኛል። በዚህም የሴቶችን የስራ ጫና በማቃለል ትርጉም ያለው ሚና መጫወት ጀምሯል።

በሌላ መልኩ በገጠር ሴቶች ይስተዋሉ የነበሩ የመሬት አጠቃቀም ክፍተቶች ለመቅረፍ እንዲቻል የሴቶችን የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖራቸው የሚያስችል የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት ለ11.11 ሚሊዮን (2 ሚሊዮን አማወራ እና 9.11 ሚሊዮን በጥምር) ሴቶች የመሬት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን በግብርና ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎ፣ ተጠቃሚነትና የሀብት ባለቤትነት እንዲሁም ከዘርፉ የሚያገኙት የነፍስ ወከፍ ገቢ እንዲያድግና ምርትና ምርታማነታቸው እንዲያድግ አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ አስችሏል፡፡ በተጨማሪም አሰራሩ አማወራ ሴቶች መሬታቸውን በሌሎች አካላት በመነጠቅ ረገድ የነበሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እየፈታ ይገኛል፡፡ በዋና በ2002 ምርት ዘመን ከነበረበት 202.46- በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ የምርት

መጠኑ አድጎ ወደ 274.42 ሚሊዮን ኩንታል ከፍ ሲል ምርታማነትን ደግሞ 19.14 ኩንታል በሄክታር ማድረስ ተችሏል። በዚህም ሂደት የገጠር ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት የነበረው ሁለንተናዊ ፋይዳ የላቀ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንግስት በገጠር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተለይ ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን ቤተሰቦች በሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ በማድረግ፣ ጥሪት እንዲያፈሩ በማስቻልና ከልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተመርቀው እራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ መንግስት በዘረጋው ስርዓትና ፕሮግራም ከድህነት ወለል በታች የነበሩ በርካታ ሴቶችና ቤተሰቦች መውጣት ችለዋል።

ሴቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግና ከሚያገኙት ገቢ የቁጠባ ባህል በማዳበር መቆጠብ እንዲችሉ በተሰሩ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችና ከአበዳሪ ድርጅቶች ጋር በተፈጠረው ቅንጅታዊ አሰራር 6.62 ሚሊዮን ሴቶችና 80,148 የሴት አደረጃጀቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በመሆን በአጠቃላይ ብር 2 ቢሊዮን ብድር በመውሰድ ስራ ላይ ያዋሉ ሲሆን ብር 2.82 ቢሊዮን መቆጠብ ችለዋል። በአጠቃላይ በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ ከተፈጠረው የስራ ዕድል፣ ከተመቻቸው የብድር አገልግሎት፣ ከተሰጠው ስልጠናና የገበያ ትስስር የሴቶች ድርሻ በቅደም ተከተል 41.47%፣ 40.8%፣ 39.7% እና 36.1% ደርሷል።

በከተማና ገጠር ኢንዱስትሪዎችና ኢንቨስትመንቶች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የሴቶች ተሳትፎ እያደገ በመምጣቱ በአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (GDP) ላይ በመጣው ተከታታይ የሆነ ዕድገት የሴቶች ገቢ በማደጉ ለቤተሰብ ኑሮ መሻሻልና ለሴቶች ገቢ መጎልበት ከፍተኛ ድርሻ አበርክቷል።

በገጠር፣ በከተማና በአርብቶ አደር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የተዘጋጀውን የጋራ ዕቅድ መሠረት በማድረግ ሴቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ልማትና በተለያዩ ገቢ ማስገኛ ሥራዎች በስፋት እንዲሣተፉና እንዲጠቀሙ ለማድረግ ሰፋፊ ስራዎች ተሰርተዋል።

2.2.3. ማህበራዊ ውጤቶች

በሀገራችን በሴቶች ትግል ከተገኙ ውጤቶች አንዱ ያታን መሰረት ያደረገ የስራ ክፍፍል እንዲቀር የአመለካከት ለውጥ መፈጠሩ ነው። ለምሳሌ ያህል ውሀን ለቤተሰቡ ማቅረብ በህብረተሰቡ ዘንድ ዋነኛ የሴቶች ተልእኮ ተደርጎ ስለሚቆጠር በዚህ ሳቢያ ሴቶች ረዥም ሰዓትና መንገድ በመጓዝ ጤናቸውን ከመጉዳት አልፈው ለተለያዩ የሀይል ጥቃቶች ሰለባ የሚሆኑበት አስከፊ ሁኔታ ነበር። ባለፉት ሁለት አስርት አመታት የውሃ ሽፋኑን ለማሳደግ በተሰራው ሥራ በከተማም በገጠርም በአቅራቢያ ንፁህ ዉሃ ማግኘት የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ከማንም በላይ ለሴቶች ስልታዊ ጠቀሜታና ትርጉም ያለው በመሆኑ ሴቶች ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን የሚያባክኑበት ሁኔታ ቀርቶ ሙሉ ዕውቀታቸውንና ጊዜያቸውን በምርት ተግባር ላይ እንዲያውሉ አስችሏቸዋል። ይህም ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን የስራ ድርሻ በተመለከተ የአመለካከት ለውጥ በመኖሩ እና መንግስት የውሃ አቅርቦት ላይ መሰረታዊ ስራዎችን በማከናወኑ የተገኘ ውጤት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሴቶች በማህበረሰቡ በተሰጣቸው የስራ ክፍፍል ምክንያት እለት ተእለት የቤተሰቡን ኑሮ የመምራት ሃላፊነት በእነርሱ ጫንቃ ላይ ወድቆ የነበረ ሲሆንአንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከ5-7 ሰዓት የእግር መንገድ የሚጓዙበት ሁኔታ እንዳለ ያሳያል። በዚህም ምክንያት ለተለያዩ የጤና ችግሮች፣ የሀይል ጥቃቶችና ለምርት ተግባር ቢውል የላቀ ጥቅም ሊያስገኙ የሚችሉ እድሎችን የሚጎዳበት ሁኔታ ይፈጠራል። ባለፉት አመታት በተከናወኑ ተግባራት ግን የገጠር ቀበሌዎች ክረምት ከበጋ በሚያስኬድ መንገድ የተገናኙ በመሆናቸው በአማካይ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ የሚወስደው ጊዜ በማሳጠር ወደ ሰዓታት ዝቅ ማድረግ

ተችሏል። ይህም የሴቶችን የስራ ጫና በማቃለል ረገድ ትርጉም ያለው ድርሻ ይኖረዋል።

ትምህርት የዕድገት ሁሉ መሰረት መሆኑን መንግስት በመቀበል በየደረጃው ትምህርት ለማስፋፋት ባካሄደው እንቅስቃሴ የሴቶች ተሳትፎ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። በዚህም ምክንያት በአንደኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ የሴቶች ከወንዶች የትምህረት ተሳትፎ የአንድ ለአንድ ምጥጥኑ የተሳካ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በ2009 ዓ.ም ወደ ዩንቨርስቲ ወይም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከገቡ ተማሪዎች መካከል ወደ 42 ከመቶ የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸው እንዲሁም በአጠቃላይ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ከአንደኛ አመት ጀምሮ ተመራቂ እስከሆኑት ተማሪዎች ሴቶች 38 ከመቶ የሚይዙ መሆኑ ሲታይ በትምህርት መስክ የተሰራው ስራ ምን ያህል ሴቶችን ተጠቃሚ ያደረገ መሆኑን በተጨባጭ የሚያመለክት ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዩንቨርሲቲዎች የሴት መምህራን ሴት አመራሮችን ለማፍራት በተደረገው ጥረትም 20 ከመቶ ማድረስ መቻሉ በተጨማሪነት የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የተሰራውን ስራ በግልፅ የሚያያሳይ ሀቅ ነው።

በጤናው ዘርፍ በሽታን መከላከል መሰረት ያደረገውን የጤና ፖሊሲ በብቃት ለመተግበር ከ40,000 በላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የተሰማሩ ሲሆን የእናቶችና ህፃናትን ሞት በመቀነስ ሂደት አበረታች ውጤቶችን ማስመዝገብ ተችሏል። በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና ጾታዊ ጥቃቶችን ለመቀነስ የህብረተሰቡን ግንዛቤና አመለካከት ከማሳደግ ባሻገር መንግስት በወሰደው የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎች ማሻሻያ እርምጃዎች የሴት ልጅ ግርዛት ከነበረበት 37.7% ወደ 23%፣ ጠለፋ ከ23.3% ወደ 12.7%፣ ያለዕድሜ ጋብቻ ከ21.4% ወደ 8% ቀንሷል።

2.3 ሴቶችና ቁጠባ

ሴቶች በተለያዩ ጊዜያት ካጋጠምዋቸው ጭቆናዎች ታግለው በመውጣት ካስመዘገቡት ድል ውስጥ አንዱ የሴቶች የቁጠባ ባህል ማደግ ነው። ብዙ ሴቶች የቁጠባ አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆን የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ኑሮ መለወጥ እየቻሉ ነው። ይህም ልጆቻቸውን ያለችግር ከማስተማር ባሻገር ለኑሯቸው የሚሆን ቁሳቁስ ለማሟላት እያገዛቸው ነው። በተለይ ሴቶች ከተቀጣሪነት በመውጣት በራስ ጥረት ለመኖር የሚያደርጉትን ትግል መንግስታችን በተለያየ አግባብ እየደገፈ ይገኛል። ለአብነትም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል የተጀመረው አገልግሎት አንዱ ማሳያ ነው። በተጨማሪም የሴቶችን የቁጠባ ባህል ለማሳደግ በገጠርና በከተማ የተለያዩ ማይክሮ ፋይናንሶችና ሌሎች አማራጮ በብዛት ተደራሽ ሆነዋል ።

የቁጠባ ባህልን በማሳደግ ሴቶች በቤተሰቦቻቸው፣ በአካባቢያቸውና በማህበረሰቡ ዘንድ የጐላ ሚና አላቸው በተለይም የሴቶች የልማት ቡድን አደረጃጀት ከተጀመረ በኋላ ትልቅ አምርታዊ ለውጥ እየተመዘገበ ይገኛል። ይህም በሀገር ደረጃ ልናስመዘግባቸው ለምንፈልጋቸው ትልልቅ ድሎች ጠንካራ መሠረት እየሆነ ይገኛል። በዚህም ምክንያት ወደ 2.82 ቢሊዮን ብር በአንደኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽናል አቅድ ዘመን መቆጠብ ችለዋል። ሆኖም ግን የሴቶች የቁጠባ ባህል አሁንም በሚፈለገው ደረጃ ማደግ እንዳልቻለ መረዳት ይቻላል።

2.4. በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሲበሰርና የመሰረት ድንጋይ መጋቢት 24/2003 ዓ/ም ሲጣል የህብረተሰባችን ግማሽ አካል እና የእያንዳንዱ ቤተሰብ ምሰሶ የሆኑት ሴቶች በግንባር ቀደምትነት በመሰለፍ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፋቸውን ገልጸዋል።

ህዝባዊ ድጋፉ ወደ ተግባር ሲቀየር፣ በቦንድ ግዢና በተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች በግንባር ቀደምትነት በመሳተፍ ለግድቡ ገቢ በመስጠት እና በማሰባሰቡ ረገድ ሴቶች ከፊት ተሰልፈው ሃገራዊ

ሚናቸውን በመወጣት ላይ ናቸው፡፡ በግድቡ ግንባታ ላይ በሰውቀት እና በጉልበት ተሰማርተው ከሃለፊነት ጀምሮ በሁሉም የስራ መስክ በማገልገል ላይ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በግላቸው በመተዳደር በታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ስፍራ እና በግድቡ መስመር ላይ በሚገኙ ከተሞች የተለያዩ አገልግሎቶች በመስጠት ራሳቸው እና በግድቡ ስራ ላይ የተሰማሩ ወገኖቻችንን በመጥቀም ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ለግድቡ አካባቢ ድምቀትም ህይወትም በመሆን ራሳቸው ተጠቅመው ሃገራቸውንም በመጥቀም ላይ ይገኛሉ፡፡

የአገራችን ሴቶች ለግድቡ ገቢ ከማሰባሰብ ጎን ለጎን የቁጠባ ባህላችንን በማዳበር ላይ በሚገኘው በታላቁ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ግዢ በመፈጸም ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ድጋፍ በማጠናከርም ሆነ ለሃገሪቱ የቁጠባ ባህል መዳበር እያደረጉት ያለው አኩሪ ተግባር ታሪክ የሚዘክረው ነው፡፡

በአገሪቱ የአርሶ አደር እና አርብቶ አደር አካባቢዎች ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ በሚሰራው የአካባቢ እንክብካቤና የአፈር ጥበቃ ስራ ሴቶች በመሳተፍ የበኩላቸውን ድጋፍ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ በዚህም ግድቡ በደለል እንዳይሞላ የገጠሯ ሴት የእርከን ስራዎች ላይ ጉልበቷን በማፍሰስ እየጎለበቱ ባሉ ምንጮችም ተጠቃሚ እየሆነች ነው፡፡

በዲፕሎማሲው እና በፐብሊክ ዲፕሎማሲው ረገድም ከጎረቤት እና ሌሎች አገራት ጋር ያለን ግንኙነት እንዲጠናከር የበኩላቸውን ሚና እየተጫወቱ ነው፡፡ ግድባችን ሲጠናቀቅ ከጎረቤት አገራት ጋር በሚኖረው የኃይል ትስስር ምክንያት በሚፈጠረው ሰላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ ቀጠና የሰላሙ እና የኢኮኖሚ ትስስሩ ውጤት ተጠቃሚ ከመሆናቸውም በላይ በቀጠናችን ብሎም በአህጉራችን አፍሪካ አንድ የጋራ ኢኮኖሚ ለመገንባት በሚደረገው ሂደት ግንባር ቀደም ተዋናይ እንደሚሆኑ ከአሁኑ አመላክቷል፡፡

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሩጫ በዓለም ዓቀፍ የሴቶች ቀን ጋር ተሳስሮ እንዲካሄድየተደረገበት አብይ ምክንያት ሴቶች ለህዳሴ ግድቡ ያላቸውን ተሳትፎ አጠናክረው እንዲቀጥሉ እና ለሴቶች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት የሚኖረውን ፋይዳ ለማስገንዘብ ሲሆን ግድቡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሴቶች አኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚከተሉት ፋይዳዎች እንደሚኖሩት ይታመናል፡፡ እነዚህም፡-

- በታላቁ ህዳሴ ግድብ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ምክንያት ኢንዱስትሪዎቻችን በስፋት መጠናከር ሲጀምሩና ሲስፋፉ ሴቶች የኢንዱስትሪ ባለቤት፣ ሰራተኛ በመሆን እና የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በማከፋፈል በተደራጀ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ስራዎች መሰማራት እንዲችሉ ከፍተኛ አገዛ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በሀገራችን ማህበራዊ ፍትህ እንዲሰፍን ይረዳል፣
- በገጠርና በከተማ መሰረተ ልማቶችና የተለያዩ አገልግሎቶች እንዲሟሉ (የጤና፣ ትምህርት፣ የስራ ጫና ማቃለያ ቴክኖሎጂ ወዘተ...) በማገዝ ሴቶች በሁሉም ዘርፍ ጤጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ለምሳሌ በምርታማነት ስራ እንዲሰማሩ ያስችላቸዋል፣
- በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶችን አስመልክቶ ያለውን የተዛባ የስርዓተ-ጾታ አመለካከት እንዲለወጥና የወንዶች አጋርነት እንዲጎለብት ያደርገዋል፣
- የአርሶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር እንዲሁም በጥቃቅንና አነስተኛና በትላልቅ ኢንዱስትሪዎች የተሰማሩ ሴቶችን ምርትና ምርታማነት እንዲያሳድጉ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፣
- ሀገራችን ሴቶችን አስመልክቶ የገባቻቸውን ቃል ኪዳኖችና የልማት እቅዶች ለማሳካት ያስችላታል፣

2.5. የአረንጓዴ ልማትና የከተማ ውበት

ጽዱና የከተማ አረንጓዴ ልማት ለሴቶች የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ሁለንተናዊ ሚና አለው፡ ፡ የከተማ አረንጓዴ ልማት ሲባል እቅድ ወጥቶላቸው የህብረሰተቡን ፍላጎት መሰረት በማድረግ

የሚለው አረንጓዴ ቦታዎች፡ ጋርደኖች ፓርኮችና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን የሚያጠቃልል ነው፡ ፡ በዚህም ረገድ ሴቶች የአረንጓዴ ልማት ተግባራት በመሳተፍ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡፡ ሌላው በሁሉም ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አሰባብ፡ አወጋገድና መልሶ የመጠቀም ተግባር ትልቅ ተግዳሮት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ቆሻሻዎችም ከመኖሪያ ቤት፣ ከንግድ ቤቶች፣ ከግንባታዎችና ከተቋማት የሚመነጩ ናቸው ይህም በሴቶችና በመላ ህብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ የሆነ የጤናና የስነ አህምሮ ችግሮች እያደረሰ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ሴቶች በመኖሪያ አካባቢያቸው ቆሻሻዎች በማሰባሰብና በማጽዳት እንዲሁም በማስወገድ ረገድ የበኩላቸውን ሚና መወጣት አለባቸው፡፡ በሌላ በኩል መስኩ ለሴቶች የስራ እድል ስለሚፈጥር አሟጦ መጠቀም ያስፈልጋል፡

2.6 ሴቶችና የልማት ቡድን

በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ በርካታ ሴቶችን ያቀፉ የሴቶች ልማት ቡድኖች እና የ (1ለ5) የሴቶች ኔትዎርኮችን አደራጅቶ ወደ ተግባር በማስገባት የእናቶችንና የህፃናትን ሞት፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና የሀይል ጥቃቶችን በመቀነስ፣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ በማድረግ፤ ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱና ትምህርታቸዉን እንዳያቋርጡ በማድረግ፣ ተግባር ተኮር ትምህርትን በመከታተል፣ በግብርና ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ መስኮች በመሰማራት እንዲሁም በተፈጥሮ ሃብት ልማት በንቃት በመሳተፍ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ሆኖም ግን አብዛኛው የሀገራችን ሴቶች በልማት ቡድኖች ያልታቀፉበት ሁኔታ አሁንም ስላለ በዚህ ረገድ መስራት ያስፈልጋል፡፡

2.7. ሴቶች ሰላምና ዲሞክራሲ

ባለፉት ሁለት አስርት አመታት በተደራጀ አግባብ ሴቶችን በማሳተፍ፣ የህዝብ አቅምን የማዕዘን ድንጋይ በማድረግ፣ ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል መሰረተ ሰፊ፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት፣ መሰረተ ፅኑ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲሁም ማህበራዊ ፍትህን ለማምጣትና ልማታዊ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችሉ ዘርፈ-ብዙ ተግባራት ሲያከናውን ቆይቷል እያከናወነም ይገኛል፡፡ በዚህም አግባብ በሁሉም ዘርፍ ትልቅ አምርታዊ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡

ይሁን እንጂ የተፈጠረውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ልማት የሚገዳደሩ በሀገር ውስጥና በውጪ ምክንያቶች በተለያዩ አካባቢዎች የህብረተሰቡን ሰላም የሚያደፈርሱ ሁከቶች በየጊዜው ብቅ ጥልቅ የሚሉበት ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡በአንድ ሀገር ሰላም በማይኖርበት ወቅት የመጀመሪያ ተጎጂዎች ሴቶች በመሆናቸው (ለምሳሌ ያህል ሴቶች ለጥቃትና ለሌሎች ኢሰብዓዊ ድርጊቶች ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል) ለሰላም ዘብ መቆም ብሎም የሁከትና ብጥብጥ ምክንያቶችን ከምንጩ ለማድረቅ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ለሀገራችን ሴቶች ጉዳይና ለብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና ጥቅም ትልቅ ትኩረት በሰጠው የቃል ኪዳን ሰነድ በሆነው ህገ መንግስት ሁሉም ዜጎች የተጎናፀፉትን የመምረጥና የመመረጥ መብት በመጠቀም መሳተፍ እንደሚችሉ እውቅና ተሰጥቷል፡፡ በዚህም መሰረት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ዜጎች የፈለጉትን ፓርቲ በመምረጥ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የበኩላቸውን እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ረገድ ሴቶች የአንበሳውን ድርሻ እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ በቀጣይም በሀገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የበለጠ እንዲጎለብት የበኩላቸውን ሚና መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

“መልካም አስተዳደርን በማስፈን የሴቶችን እኩል ተሳትፎ ተጠቃሚነት እናረጋግጥ!”
41ኛ
አለም አቀፍ የሴቶች ቀን–ማርች 8
የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም
106ኛ
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር

ለአገራችን የሀዳሴ መሰረትና ድልድይ ሆኖ እያገለገለና ለሴቶች ሁለንተናዊ ችግሮችና የኑሮ ሁኔታ መሻሻልም ትልቅ አስተዋፅኦ እያበረከተ ያለውን የሴቶች የልማት ቡድን የማጠናከርና ባልተቋቋመባቸው እንዲቋቋም ማድረግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

3.3. ማጠቃለያ

የሴቶችን ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ለማረጋገጥ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር በርካታ ርቀቶችን የተጓዘ ሲሆን በዚህም ሴቶች በየደረጃው ባሉ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ የሀገራቸውን ሀዳሴ ማስቀጠልና ራሳቸውን መጥቀም ችለዋል፡፡ የቃል ኪዳን ሰነድ የሆነው ሀገ መንግስት እና ይህን ሕገ-መንግስት በጽኑ እምነት በመተግበር ላይ የሚገኘው መንግስት በሴቶች ላይ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስኮች ሲደርስባቸው የነበሩት በደሎችን እና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለማስተካከል በወሰዳቸው እርምጃዎች መጠነ ሰፊ ውጤቶች ሊመዘገቡ ችለዋል፡፡

በዚህም የሴቶች እኩል ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፣ በሴቶች ላይ ሲደርሱ የነበሩ በደሎች እና መገለሎች እንዲሁ በጊዜ ሂደት እየቀነሱ የሄዱበት ሁኔታ በስፋት ይስተዋላል፡፡ ይሁንና እስከ አሁን የተመዘገቡት ውጤቶች እንደተጠበቁ ሆነው ውጤቶቹ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በሚፈለገው ደረጃ እና ጥልቀት መጠን እንዲመጣ ከማድረግ አንፃር ወደ ፊት ሰፊ ስራዎችን ማከናወን የሚጠበቅብን ይሆናል፡፡

ስለሆነም ሀገ-መንግስታዊ ስርዓቱን እየተፋታተኑ ያሉ ጉዳዮች ላይ ያለሰለሰ ትግል በማካሄድ የሀገራችንን ሀዳሴ ለማረጋገጥ እንዲቻል የሴቶች ተሳትፎ እና ቁጠባ ባህል ማደግ ወሳኝ በመሆኑ በዚህ ላይ ጠንካራ ትግል ማካሄድና ውጤታማ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅብናል፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን የተገኙ ውጤቶቻችን ረጅም ርቀት የወሰዱን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁንም የሚቀረን መንገድ ረጅም ጉዞ የሚፈልግ ነው። የተጀመረው የመዋቅር ለውጥ ጉዞ እንዲፋጠን ለማድረግ የተሟላ ሀብረተሰባዊ ለውጥ ማረጋገጥ ይገባል። ይህን የሀብረተሰባዊ ለውጥ ማፋጠን በተበተነ መንገድ ሳይሆን የጀመርነው ሀገራዊ የሀዳሴ ጉዞ በአጠቃላይ የሀገሪቱ ህዝቦች አጠቃላይ ሁኔታ የሚያሻሽል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም የሴቶችን ማህበራዊ ሁኔታና ቦታ በማሻሻል ረገድም እሴት የሚጨምር በመሆኑ ይህን ታሳቢ ያደረገ እንቅስቃሴ በማድረግ በሂደቱ የሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በታቃደው መንገድ ማረጋገጥ ይገባል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

1. የሴቶችና ሕጻናት መብትና ጥቅሞችን በማስተከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡
2. የሴቶችና ህጻናትን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፤
3. ሴቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤
4. ሴቶች እንደፍላጎታቸውና እንደችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ አቅማቸውን ይገነባል፡፡
5. በፌደራል መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የህጻናትን ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፤ ይገመግማል፤ ተገቢውን ክትትል ያደርፈጋል፤
6. በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹ የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
7. በሀገር አቀፍ ደረጃ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
8. ሴቶች በተለያዩ የመንግስት አካላት በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤
9. የህጻናት መብትና ደህንነታ እንዲጠበቅ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉን ያስተባብራል፤
10. ሴቶችንና ህጻናትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችን በሕግ መሠረት ይዋዋላል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፡፡

በተጨማሪም በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ሴቶችንና ሕጻናትን በሚመለከት ለሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፡-

- ስልክ
  - 0115528394/0115525455
- ፋክስ
  - 0115522270/0115525455
- ፖ.ሣ.ቁ
  - 1293 አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
- ኢ. ሜይል
  - mowca.affairs@gmail.com
- ድረ-ገጽ
  - http://www.mowcya.gov.et
- ፌስቡክ
  - ministry of women and children affairs
- ቲውተር - Twitter / MOWCA2

41ኛ አለም አቀፍ የሴቶች ቀን — ማርች 8 106ኛ

የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም

“የሴቶች የቁጠባ ባህል ማዳግ ለህዳሴያችን መሰረት ነው!!”

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር

Shampion printing press
Tell 0911237322